አወንታዊ ፣ አሉታዊና መጠይቃዊ ዓ.ነገሮች

- <u>አወንታ</u> ማለት ደጋፊ፣ የዓ.ነገሩን ሀሳብ የማያፈርስ ማለት ነዉ
- አወንታዊ ዓ.ነገር መጨረሻ ላይ ያለዉ ቃል የማያፈርስ ከሆነ ዓ.ነገሩ አወንታዊ ዓ.ነገር ነዉ።

  ምሳሌ፦ ልጁ ኳስ <u>ተጫወተ</u>።

  ልጅቷ ቁርሷን <u>በላች</u>።

  ከዚህ በላይ ባሉት ዓ.ነገሮች ያሉት የተሰመረባቸዉ ቃላት አፍራሽ ቃላት ስላልሆኑ ዓ.ነገሮቹ አወንታዊ ዓ.ነገሮች ናቸዉ።
- <u>አሉታ</u>- ማለት አፍራሽ ማለት ነዉ፦
- አሉታዊ ዓ.ነገር መጨረሻ ላይ ያለዉ ቃል አፍራሽ ቃል ከሆነ ዓ.ነገሩ አሉታዊ ዓ.ነገር ነዉ።

  ምሳሌ፦ ልጁ ኳስ አልተጫወተም።

  ልጅቷ ቁርሷን አልበላችም

  ከዚህ በላይ ባሉት ዓ.ነገሮች ያሉት የተሰመረባቸዉ ቃላት አፍራሽ ቃላት ስለሆኑ ዓ.ነገሮቹ አሉታዊ ዓ.ነገሮች ናቸዉ።
- <u>መጠይቃዊ ዓ.ነገሮች</u> ምላሽ የሚሹ ዓ.ነገሮች ናቸዉ። በጥያቄ መልክ የሚቀርቡ ናቸዉ።

  ምሳሌ፦ ምን ትወጃለሽ ?

  ከማን ጋር ትኖራለህ?

  መቼ ትመጣላችሁ?

  እነዚህ ከላይ ያሉት ዓ.ነገሮች መጠይቃዊ ዓ.ነገሮች ናቸዉ።

<u>መልመጃ አንድ</u>

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ እዉነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።</u>

_____1. ሰሚራ መጣች። ይህ ዓ.ነገር አሉታዊ ዓ.ነገር ነዉ።

_____2. አወንታ ማለት አፍራሽ ማለት ነዉ።

_____3. መጠይቃዊ ዓ.ነገሮች ምላሽ የሚሹ ዓ.ነገሮች ናቸዉ።

_____4. ስንት አመትህ ነዉ? የሚለዉ ዓ.ነገር መጠይቃዊ ዓ.ነገር ነዉ።

_____5. ዓ.ነገሩ መጨረሻ ላይ ያለዉ ቃል አፍራሽ ከሆነ ዓ.ነገሩ አሉታዊ ዓ.ነገር ነዉ።